# ክፉዎችን ለማሸነፍ፣ ብዙሐን በጎ ዜጎች ማሕበራዊ ሚዲያን በበጎ ስልት ማጥለቅለቅ አለባቸው

አንድነት ይበልጣል - ሀዋሳ ታህሳስ 2012

*(ክፉዎች የሚለው ቃል ሰፊ እሳቤን ሊወክል ቢችልም፣ ለዚህ ጽሁፍ ዓላማ ግን ለአሰርታት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ሲጎዱ ለኖሩ አሁንም ለማፍረስና ለመበተን እንቅልፍ አጥተው የሚሰሩትን የትህነግ ጽንፈኞችና በመላ ኢትዮጵያ ያሰማሯቸው ጀሌዎቻቸውን፣ ጀዋርና ጀሌዎቹን እንዲሁም በመንግሥትና በገዢው ፓርቲ ውስጥ አደፍጠው የሚያሴሩ ቀልባሾችን ሁሉ ሊገልጽ ይችላል።)*

ዋናው ችግር፤ ከኛ በአመለካከት፣ በእምነትና በአቋም የተለየ ሰውን ምክንያታዊ ሆኖ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ መስደብና ለማሸማቀቅ መሞከር ትልቅ ነውር ነው፤ አለመብሰልንም ያሳያል። ይባስ ብሎ ስድብና ማዋረዱን ወደማይመለከታቸው የቤተሰብ አባላት በተለይ ልጆች ጋር ለመውሰድ መሞከር ደግሞ ኃላፊነት የጎደለው የጭካኔ ተግባር ነው። ይህን መሰል ባህርይና አቀራረብን መገለጫቸው ያደረጉ ሰዎችና ቡድኖችም በራስ ወዳድነት የሰከሩና በዛሬና በነገ ተስፋ የቆረጡ ክፉዎች ናቸው። ከክፉዎች ጋር አብሮ መስከርና መባለግ በጊዜያዊነትም ቢሆን የሚጠቅመው እነርሱን ብቻ ነው። በስልትም ሆነ በግብ አንጻር የሚጠቅመው እነርሱን ነው። "የትም ፍጭው ዱቄቱን ብቻ አምጪው" እዚህ ላይ አያዋጣም። አንደኛ፣ በጎ ሰው በማያውቀው በነውረኞች ስልት ሲጫወት ጨዋታውን ማሸነፍ አይችልም። ምክንያቱም የነውረኝነቱን ሥልት አይችለውም። እንኳን በማንችልበትና የተሻለ በምናውቀውም ስልት ብንታገላቸው ክፉዎች ብዙ ፈተና ይጋርጡብናል። ሁለተኛ፣ የሚያሻግር ሃሳብ ከሌላቸውና ተስፋ ከቆረጡ ጋር እየተሰዳደቡና እየተበሻሸቁ ከመቀጠል የሚጠቀሙት መጥፎዎችና አጥፊዎች ናቸው። የነርሱ ግብ ማጣላት፣ ማፍረስና መበታተን ነው፤ መጨረሻቸው የራሳቸው መጥፋት ቢሆንም እንኳ መጣላትና ማጣላትን አይተዉም።

ከባለጌዎች ጋር በነርሱ መንገድ መዘላለፍ የሥነምግባር የበላይነታችንንና የመንፈስ ልዕልናችንንም ያስነጥቀናል። መዘላለፍ፣ ለተከታታዮቻችን ልናስተላልፍ የምንችለውን በጎና ተሻጋሪ የሆነ አማራጭ ሀሳብ ይደብቅብናል፣ የማስተማር ዕድላችንን ያሳጣናል። ክፉዎች እንዲገኑ ዕድል ይሰጣል። በመጨረሻም በጎ ሰዎች የማንፈልገውንና የሚጎዳንን፣ ክፉዎች ግን ዞሮ ዞሮ ባይጠቅማቸውም አሁን ግን የሚፈልጉትን ውጤት ለማየት እንገደዳለን (ያውም ብንኖር)። ሐገር ይፈርሳል ሕዝብ ይበተናል።

እንደኔ፣ ለተሳዳቢዎች፣ ለክፉዎችና ለአፍራሾች ተገቢ የሚመስለኝ ምላሽ አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ በዝምታ ማለፍ አይደለም። ወይም ክፉዎችን ፈርቶና ተጠይፎ ከማኅበራዊ ሚዲያ ጨርሶ መራቅም መፍትሔ ሊሆን አይችልም። የዘመኑ ስጦታ የሆነውን ማኅበራዊ ሚዲያ መዝጋትም ከፍተኛ ጉዳት አለው። ሁሉም የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ነው ባይባልም 70 በመቶ የሚሆነው ዜጋችን ወጣት መሆኑንም አንርሳ! የጥላቻ ንግግርን የሚቀጣ ሕግ መቅረጽም በቂ አይሆንም።

ለኔ ተገቢ የሚመስለኝ የመፍትሔ እርምጃ፣ አቅሙና ዕድሉ ያላቸው በጎ ዜጎች በብዛት ወደማሕበራዊ ሚዲያው መምጣትና መድረኩን በበጎና ጠንካራ ሀሳቦችና መልእክቶች በማጥለቅለቅ ክፉዎችን "አየር ማሳጣት" ነው። ክፉዎች ጥቂት ቢሆኑም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያለማቋረጥ ስለሚጮሁ ብዙኃን መስለው ይታያሉ። በጎ ሰዎች ደግሞ ብዙሐን ቢሆኑም የዳር ተመልካችነትን ስለመረጡና ድምጻቸውም ስለማይሰማ አናሳ መስለው ይታያሉ። ይህ መልሶ ብዙሐኑን እያደናገረ ተስፋ ያስቆርጣቸዋል። ስለዚህ ዲጂታል ወያኔን፣ እነጃዋርና መሰሎቻቸውን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የመታገሉን ዕዳና ስቃይ፣ ስዩም ተሾመን ለመሰሉ ጥቂት ጎበዞች ብቻ ትቶ ትልቅ፣ ፈጣንና ጠቃሚ ውጤት መጠበቅ ሞኝነት ነው። የሚያዋጣን አቅማችን በሚፈቅደው ልክ በማሕበራዊ ሚዲያው ላይ በስፋትና በቀጣይነት በመገኘት ድምጻችንን ማሰማት፣ ፍላጎታችንንና ምርጫችንን ሳናፍርና ሳናመነታ፣ በግልጽና በቁርጠኝነት ማሳወቅ፤ ክፉዎችም በርግጥም ጥቂቶች መሆናቸውን እኛም በጎ ፈላጊዎች ብዙሐን መሆናችንን በግልጽ አሳይተን በቃ ማለት መቻል ነው። ኃይል ተጠቅሞ የሕግ የበላይነት እንዲያሰፍንና ዜጎችን እንዲጠብቅ የምንወተውተውን መንግሥት፣ ምናልባትም ሳይወድ ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል ወደሚጠቀም አምባገነን እንዳይቀየር የምንረዳው የትግል ድርሻችንን በመወጣት ብቻ ነው። ዋና ባለጉዳይ ዜጎችና ሕዝብ እንደመሆናችን መጠን የድሉን ብቻ ሣይሆን የትግሉን ባለቤትነት (ኃላፊነት) በፍጥነት በእጃችን ማስገባት አለብን። መንግሥት ከጎናችን እንደሚሰለፍና የራሱንም ሥራ እንደሚሠራ አምናለሁ። እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጠን!!